Australian Government

COVID-19 VACCINATION

# ስለ COVID-19 ክትባቶች እንዴት ለህጻናት ማነጋገር እንደሚቻል

በመጨረሻ ወቅታዊ የሆነበት: ቀን 8 ነሐሴ/August 2022 ዓ.ም

እንዲሁም እድሚያቸው ከ6 ወራት እስከ 4 ዓመት ለሆኑት እና ከባድ የበሽታ መቁቋም ሀይላቸው ለተዳከመ፤ ወይም የአካል ጉዳት ላለባቸው አንዳንድ ህጻናት እንዲሁም ለከባድ COVID-19 ችግር መጨመር ለሚያጋልጥ የተወሳሰበ እና/ወይም ብዙ የጤና ችግር ላለባቸው ህጻናት ክትባቶችን እንዲወስዱ ይመከራል። ልጅዎ መጨነቅና ስለ COVID-19 ክትባት መውሰድ ብዙ ጥያቄዎች ማቅረብ የተለመደ ነው። አንዳንድ ህጻናት ስለ COVID-19 ክትባት መውሰድ ሊጨነቁ ይችላሉ። ልጆችዎ ክትባቱን ከመውሰዳቸው በፊትና በኋላ ለማነጋገር ጠቃሚ ሊሆኑ ለሚችሉት አንዳንድ ምክሮች እዚህ ላይ ቀርቧል።

በድረገጽ Department of Health and Aged Care ላይ በቅርቡ ስለቀረበ የህክምና ምክር እያወቁ መቆየት ጠቃሚ ነው።

እንዲሁም ስለ COVID-19 ክትባት መውሰድ የሆነ አሳሳቢ ጉዳይ ወይም ጥያቄዎች ካለዎት ልጅዎ ክትባቱን ከማግኘቱ በፊት ከእርስዎ ክትባት አቅራቢ ወይም ሀኪም ጋር መወያየት ይችላሉ።

ልጆችዎ ስለ ክትባት መውሰድ ያላቸውን ምላሽ ማዳመጡ እና ላላቸው ማንኛውም ፍርሃት ተቀባይነት መስጠቱ ጠቃሚ ይሆናል።

- ስለ COVID-19 ክትባት እስካሁን ምን እንደምታውቅ ንገረኝ።
- ቀደም ሲል ክትባት ወስደህ ታውቃለህን?

እድሎቹ ልጅዎ ቀደም ሲል ክትባትን ማግኘት እና ችግሩ መጥፎ ላይሆን ይችል ይሆናል።

ስለ COVID-19 ክትባት ምን እንደሚያውቁ በሀቅነት የተመረኮዘና በእድሜ ትክክለኛ በሆነ መንገድ ለመግለጽ መሞከር ነው።

ማስተዋል፡ የህጻናት ስሜት ስሜት የሚፈጠረው ከጎልማሳ በሚከሰት እንደሆነ ስለዚህ ያለዎትን ፍርሃት በውስጥዎ መያዝ እንጂ ለህጻናት ማሳተፍ ትሩ ይዞታ ስላልሆነ ታዲያ ምቹ ያልሆነ ስሜትን ሊያሳድርባቸው ይችል ይሆናል።

ሀኪም ወይም የጤና ባለሙያ ለልጅዎ አንዳንድ ጥያቄዎችን እንደሚጠይቁ; ይህም ልጅዎ በክንዱ ላይ (እድሜ ከ 6 ወር እስከ 5 ዓመት በታች ለሆኑት በእግር ላይ) መርፌ እንደሚሰጠውና ከዚያ በኋላ ትንሽ ህመም እንደሚያመው ግልጽ ማድረግ ነው። በልጆች ክንድ ላይ መጠነኛ ትንሽ ህመም መፈጠር የተለመደ እንደሆነ ለልጅዎ በማሳወቅ ማረጋገጥ እና መርፌ በተወጋበት ቦታ ላይ መታመም ማለት ይህ ማለት የተሰጠው ህክምና የሚሰራ ስለመሆኑ ያረጋግጣል።

ልጅዎ ስለ ክትባት መውሰድ ፍርሃት ካለበት፤ ስላላቸው ስሜት ለማጣራት እንዲነግርዎት መሞከር ወይም አስፈላጊ ከሆነ ከሀኪምዎ በበለጠ ምክርን መጠየቅ ነው።

## ለልጅዎ ጥያቄዎች መልስ መስጠት

ልጅዎ ሊኖረው ለሚችል ማንኛውም ጥያቄዎች እንደ የልጅ-ጓደኛማ ሆኖ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ መሆን። በዚህ ንግግር ላይ ሊረዳዎ የሚችሉ አንዳንድ ቁልፍ ጥያቄዎችና መልሶች እዚህ ላይ ቀርቧል:

ትክክለኛ ናሙናዎች መጠቀም፤ እንደ የልጅን አያቶችን ስለመከላከል እንዲሁም ይህ የሚረዳ መስሎ ከታየዎት በቀጣይነት ወደ ትምህርት ቤትና ወደ ስፖርቲ ቡድን መሳተፍ የመሳሰሉትን መቀጠል እውንዲቻል ማድረግ ነው።

አውስትራሊያ ውስጥ የሁሉም ክትባቶች ደህንነት የተጠበቀ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ በድርጅቶች በኩል ሙሉ በሙሉ ምርመራ ተካሂዷል። ደህንነታቸው ያልተጠበቀ ቢሆን ኑሮ ለሰዎች መሰጠት አይችልም ነበር።

ልጅዎ መርፌ መወጋት የሚፈራ ከሆነ፤ ለዚህ ጥሩ ዝግጅት ማድረግና ለመፍራት ተከኒካል ዘዴ ማውጣቱ ጠቃሚ ነው።

እድሜያቸው 5 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑት ህጻናት ይህ ልጅዎ በትንሽ፤ በጣም በሚያውቀው ቦታ፤ ማለት በአካባቢ ፋርማሲ ወይም አጠቃላይ ሀኪም፤ ከፍተኛ መጠን ክትባት በሚሰጥበት ቦታዎች ላይ ከፍተኛ ድምጽና የሥራ ብዛት ባለበት ቦታ የመረባበሽ ችግር ሊጨምር ይችል ይሆናል።

ልጅዎ ለሚወደው አሻንጉሊቶች ወይም መጽሀፍት ይዞ በመምጣት አወንታዊ የሆነ ተመኩሮ ስሜትን ለመፍጠር ነው።

ልጅዎ መርፌ መወጋትን የሚፈራ ከሆነ ቀደም ብሎ ለእርስዎ ክትባት አቅራቢ በማሳወቅ ይህን ማቀናጀት እንዲችሉ በቂ ጊዜ እንደሚኖራቸውና የአሰራር ሂደቱ በማጣደፍ ወይም በማስገደድ እንዳይሆን ማረጋገጥ ይቻላል።

የበለጠ መረጃ ከፈለጉ ለ Department of Health and Aged Care ወብሳይት በድረገጽ www.health.gov.au ላይ በመግባት ስለ ክትባት ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

እንዲሁም ለ National Coronavirus እና COVID-19 Vaccine Helpline በስልክ **1800 020 080** መደወል ይችላሉ። ለነጻ አስተርጓሚ አገልግሎቶች ምርጫ ቁጥር 8'ን መጫን።

ደንቆሮ ወይም የመስማትና መናገር ችግር ካለብዎት ለአገር አቀፍ መቀባባያ ኣገልግሎት/National Relay Service በስልክ **133 677** አድርጎ መደወል ይችላሉ።